# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 72 መስከረም 21 2001 ዓ.ም


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

> አገራችን፣ ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ የምርጫ ውጤት ካልተስማማው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚያውጅባት፣ በመለስ ትእዛዝ ሰላማዊ ስልፈኞችን እያነጣጠረ ግንባርና ልብ ላይ የሚተኩስ ነብሰ ገዳይ፣ ልዩ ጦር መኖሩ በግልጽ የታየባት አገር ናት።

## “አገሬን ከሚመጣው አደጋ ለማዳን ስል እርምጃ መውሰድ ነበረብኝ” ጄ/ል ተፈራ ማሞ

በመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ተከሰው በወያኔ እስርቤት እየማቀቁ የሚገኙት ጀግናው የጦር አዛዥ፣ ጄ/ል ተፈራ ማሞ፣ “አገሬን ከሚመጣው አደጋ ለመከላከል ስል የግድ እርምጃ መውሰድ ነበረብኝ” ሲሉ በችሎቱ ላይ ለተሰየሙት አሻንጉሊት ዳኞች ተናግረዋል።

በወያኔ የጦር አዛዦች ዘንድ ሳይቀር በጀግንነታቸው የሚታወቁትና በሰራዊቱ አባላት ዘንድ ተወዳጅ የሆኑት፣ ጄኔራል ተፈራ ማሞ፣ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት በአንድ ብሄር ቁጥጥር ስር ሙሉ በሙሉ መውደቁን፣ ከትግራይ ብሄር ውጭ ያሉት የሌሎች ብሄሮች የጦሩ አባላት እንደ ሁለተኛ ዜጋ እንደሚቆጠሩና ይህም ህገ ወጥ አሰራር ለአገሪቱ አንድነትና ህልውና አደገኛ መሆኑን የወያኔ ተላላኪዎች ለሆኑት አዲሱ ለገሰና ተፈራ ዋልዋ ገልጸውላቸው እንደነበር ለፍርድቤቱ ተናግረዋል።

የጄ/ል ተፈራ ንግግር በተመሳሳይ ክስ ተከሰው ለሞት የተዳረጉትን የ ጄ/ል መንግስቱ ንዋይን ንግግር የሚያስታውስ ሲሆን፣ ጄ/ል መንግስቱ በስቅላት እንዲቀጡ ሲፈረድባቸው “ እኔ ብፈልግ በየቀኑ መኪናዎችን መቀያየር እችላለሁ፣ በየቀኑ የተመረጡ የፈረንሳይ ሻምፓኞችን መጠጣት እችላለሁ፣ ሺዎች የንጉሱን ደጅ ለመርገጥ ወረፋ ሲይዙ እኔ ግን እንደልቤ መግባትና መውጣት እችላለሁ። ይህን ሁሉ ጥቅሜን ትቼ ግን አገሬን ከድንቁርና፣ ከድህነትና ከሁዋላቀርነት ለማውጣት ስል ይህን እርምጃ ወስጃለሁ” ማለታቸው ይታወሳል። በሁለቱ ጄኔራሎች መካከል ያለው ልዩነት አንዱ ድንቁርናንና ሁዋላቀርነትን በመቃወም መነሳቱ ሲሆን ሌላው ደግሞ ዘረኝነትን የተቃውሞው ማእከል ማድረጉ ነው። ሁለቱም የጦር መሪዎች ግለሰባዊ ምቾታቸውን ለአገራቸው ጥቅም ሲሉ አሳልፈው የሰጡ የኢትዮጵያ መኩሪያዎች ናቸው። **ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

## በተቃዋሚ, ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ላይ የሚፈጸመው ድብደባና እስራት ተባብሶ ቀጥሎአል

መድረክ የተባለው የተቃዋሚዎች ስብስብ ሊቀመንበር የሆኑት ገብሩ አስራት ባለፈው ሳምንት በሰጡት መግለጫ ከጊዜ ወደጊዜ ተስፋ እየቆረጠ የመጣው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በተቃዋሚዎች አባላትና ደጋፊዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ጥቃት መክፈቱን ተናግረዋል:: አዲሱ ዙር የወያኔ ጥቃት በዋነኝነት ያነጣጠረው በኦሮሚያና አማራ አካባቢዎች በሚንቀሳቀሱ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎች ላይ መሆኑን የተናገሩት የቀድሞ የህወሀት ከፍተኛ አመራር፣ መግለጫውን እስከሰጡበት ያለፈው ረቡዕ ድረስ ከሁለቱ ክልሎች 480 ሰዎች እንደታሰሩ መታወቁንና በሌሎችም ክልሎች ተመሳሳይ የአፈና እርምጃ ሊወሰድ እንደሚችል ሳይደብቁ ተናግረዋል::

ይህ በዚህ እንዳለ በጎጃም የሚኖሩ አንድ የአንድነት ለሰላምና ለዲሞክራሲ ደጋፊ የሆኑ አዛውንት ለመንፈሳዊ አግልግሎት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለተሰበሰቡ ምእመናን “አንድነት ጻረ ሰላም ና ጻረ ህዝብ ነው”**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## “የወያኔ ባለስልጣናት እስከዛሬ ለፍርድ አለመቅረባቸው ያበሳጨኛል”- ኮንግረስ ማን ዶናልድ ፔይን

ከግንቦት 97 ምርጫ ጋር ተያይዞ ለተገደሉት ከ 200 በላይ ኢትዮጵያውያን፣ የወያኔ ገዢዎች እስካሁን ድረስ ተጠያቂ አለመሆናቸው እንደሚያንገበግባቸው ኮንግረስ ማን ፔይን ገልጸዋል።

ኮንግረስ ማን ዶናልድ ፔይን “አፍሪካ በኦባማ ዘመን” በሚል ርእስ በዋሽንግተን ዲሲ ኮንቬንሽን ሴንተር የተደረገውን ውይይት በመሩበት ጊዜ እንደተናገሩት በኢትዮጵያ በኦጋዴንና በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች ከፍተኛ የሆነ የሰብአዊ መብቶች ረገጣዎች እየተፈጸሙ መሆኑን አውስተዋል። በተለይም ከግንቦት 97 ምርጫ ጋር ተያይዞ ለተገደሉት ሰዎች እስከዛሬ ድረስ ተጠያቂ አለመኖሩ በእጅጉ እንደሚያሳዝናቸው ተናግረዋል።

መጭው ምርጫ ነጻና ፍትሀዊ እንደማይሆን በእርግጠኝነት የተናገሩት ኮንግረስማን ፔይን፣ ወያኔ በቅርቡ ያወጣቸውን ህጎች በመጥቀስም አገዛዙ ዲሞክራሲን በማፈን በስልጣን ላይ ለመቆየት መወሰኑን አጋልጠዋል።

የኦባማ አስተዳደር የአፍሪካውያንንና የአሜሪካን ፍላጎቶች የሚያንጸባርቅ፣ ለዲሞክራሲ ግንባታና ለሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ትኩረት የሚሰጥ፣ መልካም አስተዳደርንና የኢኮኖሚ ግንባታን ማእከል ያደረገ ፖሊሲ እንደሚቀርጽም ተናግረዋል።

ግዜ

## የድንበር ጉዳይ ኮሚቴው የወያኔን የአገር ክህደት በጥብቅ አወገዘ

የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የወያኔው አገዛዝ የአገራችንን ሰፊ መሬት በመጭዎቹ ጥቂት ቀናት ለሱዳን ለመስጠት መወሰኑን ተከትሎ ጠንካራ የውግዘት መግለጫ አውጥቷል፣ ኢትዮጵያውያንም እርምጃውን እንዲቃወሙት ጥሪ አቅርቧል።

ኮሚቴው መስከረም 16፣ 2002 ዓም ባወጣው መግለጫ “ሱዳኖች ብሄራዊ በሆነና የመንግስት ተቋማትን፣ የዜና አውታሮችን፣ የጦር አባላትንና ህዝቡን ባስተባበረ መልኩ ዝግጅቱ እያጡዋጡዋፋት ነው፤ በኢትዮጵያ በኩል ግን የወያኔ አገዛዝ ዘርፎች የሆኑ የዜና አውታሮች የተነፈሱት ነገር የለም። በኢትዮጵያ ውስጥ በኢትዮጵያ ላይ የሚዶለተው ሴራና ክህደት እየተካሄደ የሚገኘው በከፍተኛ ሚስጥር ነው” ሲል ገልጿል።

መግለጫው አያይዞም “ ወያኔ ለሱዳን ያቀረበው ገጸ-በረከት ከሁመራ እስከ ገሙ ጎፋ ጫፍ ድንበር ያለውን ርዝመቱ 1600 ኪ.ሜ የጎን ስፋቱ ከ30 እስከ 60 ኪሎ ሜትር የሚደርሰውን ለምና ውሀ ገብ መሬትና በዚያው የሚገኙትን ደንና ብርቅየ አውሬዎችን ብቻ ሳይሆን በሰሜን ምእራብ የሚገኙትን ሁለት አንጋፋ ወንዞችን ሸንፋና ጎንግን ጭምር ነው። ይህ የወያኔ ክህደት ግብጽና ሱዳን የአባይን ራስ ለመቆጣጠር የሚያስችላቸውን ታሪካዊ ምኞታቸውንና ህልማቸውን ባልጠበቁት ወቅትና ስልት እውን እያደረግላቸው ነው” ይላል።

ኮሚቴው በሶስት የተከፈሉ ጥሪዎችን ለኢትዮጵያ ህዝብ ያስተላለፈ ሲሆን “በውጭ አገር የሚኖሩት በስልክ፣ በኢሜል ፣ በሬዲዮና በሌሎች በሚቻሉ መንገዶች ክህደቱን ማሳወቅና እነርሱም ይህን የአገር ክህደት በሚመለከት ድርሻቸውን እንዲያበረክቱ ጥሪ ማቅረብ፤ ለተባበሩት መንግስታት ፣ ለፕሬዚዳንት ኦባማ አስተዳደር፣ ለአውሮፓ ዩኒየን፣ ለአፍሪካ ህብረት፣ ለሩስያ፣ ለቻይና፣ ለደቡብ አፍሪቃ፣ ለኡጋንዳ፣ ለኬንያ፣ ለታንዛኒያና ለመሳሰሉት አገሮች በደብዳቤ ፣ በኢሜል የውሉን ህገወጥነት ማሳወቅ፣ የወያኔን መንግስት ከሃዲነት ማጋለጥና በተለይ ደግሞ በወያኔ አውታሮች ታፍኖና ተከልሎ **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## የኦርቶዶክስ አማኞች ቤ/ክርስቲያናቸውን ከወያኔ ጥቃት እንዲከላከሉ ጥሪ ቀረበ

ቤ/ክርስቲያኑዋ በቅርብ ጊዜ ታሪኳ አይታው የማታውቅ ትልቅ ችግር ከፊት ለፊቷ ተጋርጧል ሲሉ የሀይማኖት አባቶች ተናግረዋል። ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ አባቶች እንደተናገሩት ከውስጥ በኩል የወያኔ ቅጥረኛ በመሆን የሚያገለግሉት ፓትሪያሪኩ አባ ጳውሎስ፣ ከውጭ በኩል ደግሞ የወያኔ ሹመኞች በአንድ ላይ በመቀናጀት ጥንታዊቷን ቤ/ክርስቲያን ለማዳከም ሌት ተቀን በመስራት ላይ ናቸው።

አባ ጳውሎስ በቤተ- ክርስቲያኗ ውስጥ ዘረኝነትና ሙስና እንዲስፋፋ ማድረጋቸው አባቶቹ ገልጸው፣ የወያኔ ባለስልጣናት ደግሞ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ የሚያገለግሉ በተለይም የአማራ ተወላጅ የሆኑትን የሀይማኖት አባቶች ለመምታት የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ መሆናቸውን አስረድተዋል።

በተያያዘ ዜናም ሰሞኑን ለግንቦት 7 ድምጽ የደረሰው መረጃ እንደሚያመለክተው በአባ ጳውሎስና በማህበረ ቅዱሳን መካከል የተፈጠረው አለመግባባት እየተካረረ በመሄዱ ፣ በአብዛኛው ምእመንና በጥቂት የወያኔ አሽከር የሀይማኖት አባቶች ተብየዎችና ደጋፊዎቻቸው መካከል ትልቅ ግጭት ሊነሳ ይችላል ።

የወያኔ ደህንነቶች የማህበረ ቅዱሳን አባላትን ለመምታት የተለያዩ ክሶችን ማቅረባቸውን የደረሰን መረጃ ሲያመለክት፣ ከቀረቡት ክሶች መካከል ዋና ዋና ዎቹም “ማህበረ ቅዱሳን በጂማና በኢሉባቡር አካባቢ ከሙስሊሞች ጋር በተደረገው ግጭት የሞቱ ሰዎችን በጋዜጣና በሲዲ አትሞ አሰራጭቷል፣ በደሴ፣ በጎንደር፣ በባህርዳርና በአክሱም ከሙስሊሞች ጋር የተፈጠረውን ችግር ያስተባበረው ማህበሩ ነው፣ ኦርቶዶክስ አማንያን የአክራሪነት ዝንባሌ እየያዙ የመጡት በማህበሩ የህትመት ውጤቶች ነው፣ በምርጫ 97 ኦርቶዶክስ ምእመናን መንግስትን እንዲያኮርፉ አስደርጓል፣ በተለያዩ የግል ሚዲያዎች መንግስትን የሚተች ጠንካራ ጽሁፍ የሚያወጡት የማህበረ ቅዱሳን አባላት ናቸው፣ ቤተክህነት ለመንግስት እንዳትታዘዝ ወይም ተባባሪ እንዳትሆን ከሁዋላ ሆኖ ይሰራል፣ ህዝቡን በማንኛውም ሰአት ወደ ፖለቲካ ሊጠመዝዙ የሚችሉበት ሀይል አላቸው” የሚሉት ይገኙበታል።

አባ ጳውሎስም በበኩላቸው በማህበረ ቅዱሳን አባላት ላይ የተለያዩ ክሶችን ማቅረባቸውን ለማወቅ ተችሏል ። ከእነዚህም ክሶች መካከል “የማህበረ ቅዱሳን አባለት የቀድሞው ፓትሪያርክ አቡነ መርቆርዮስን **ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

## በኢትዮጵያዊያን ላይ የሚፈፀም ሰቆቃ እንዲያበቃ ወያኔን ማስወገድ ግድ ይላል

ወያኔ ሰውን በማሰቃየት የሚደሰቱ እኩይ ፍጡራን ስብስብ ነው። በረሃ ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ከእነሱ የተለየ አስተያየት የያዙ፣ አሊያም ወደፊት ይቃወሙን ይሆናል ብሎ የጠረጠሯቸውን ወዳጆቻቸውን ሳይቀር አሰቃይተዋል፤ ገድለዋልም። ከበረሃ ወጥተው መላው የኢትዮጵያን ከተሞችና ገጠሮችን በማጭበረበርም በጉልበትም ከተቆጣጠሩ በኋላም መሰሪ ሥራዎቻቸውን የሚቃወሙ ሰዎችን ማሳደድ፣ ማዋከብ እና ማሰቃየት የሰላዮቻቸውና ካድሬዎቻቸው የዘወትር ተግባር ሆኗል። በርካታ ዜጎች የወያኔ ሰው በላ አውሬዎች ሰለባ ሆነው ህይወታቸውን አጥተዋል፤ ከዚያ በቁጥር የበዙት ደግሞ ለዘላቂ የአካልና ሥነልቦና ጉዳት ተዳርገዋል። ዜጎችን ለመግደል የተደራጀው የወያኔ ቅልብ አግዓዚ ጦር በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች፤ በበደኖ፣ በአዋሳ፣ በሻሸመኔ፣ በአሰበ ተፈሪ፣ በሆሮ ጉዱሩ፣ በሀረር፣ በጋምቤላ፣ በጎንደር፣ በኦጋዴን፣ በአዲስ አበባ እና በሶማሊያ የጅምላ ጭፍጨፋና የዘር ማጥፋት ወንጀል ፈጽሟል።

የወያኔ አረመኔዎች ንፁሃን ዜጎችን እያፈኑ በየጥሻውና ጉራጉሩ ከሚያደርሱት ጥቃት በተጨማሪ "ማረሚያ ቤቶች" እያሉ በሚያቆላምጧቸው ማሰቃያዎቻቸው ውስጥ ሰቆቃ መፈጸም (ቶረቸር) ዋነኛው የምርመራ ዘዴያቸው ነው። ደርግ ሲፈጽማቸው የነበሩ የሰቆቃ ዓይነቶች ሁሉ ዛሬ ወያኔ ይፈጽማቸዋል። ከዚያም አልፎ በደርግ ጊዜ እንኳን ሥራ ላይ ያልዋሉ የሰቆቃ ዓይነቶች አሁን ተግባራዊ እየሆኑ ነው። ለምሳሌ የሰውን ጭንቅላት በሙቀት የሚያንተከትክ የኤሌክትሪክ ማጋያ መሳሪያ ደርግ አልተጠቀመም፤ አሁን ግን የወያኔ ተመራጭ የማሰቃያ መሳሪያ ነው።

በወያኔ መዳፍ ውስጥ ባሉ የፓለቲካ እስረኖች እንደ አስጊነታቸውና ታዋቂነታቸው መጠን የተለያየ ዓይነት ሰቆቃ ተፈጽሞባቸዋል። መንግሥቴን ሊገለብጡብኝ ነበር ብሎ ያሰራቸውን እነ ብ/ጄነራል ተፈራ ማሞ ላይ ብልት ቅጥቀጣ እና በኤሌክትሪክ ኃይል በሚሞቅ መሳሪያ ጭንቅላት ማጋልን የጨመሩ ሰቆቃዎች ተፈጽመውባቸዋል። ታሳሪዎች እየደረሰባቸው ስላለው ሰቆቃ ለፍርድ ቤት ተብየው በተደጋጋሚ አቤት ቢሉም ዳኞቹ ካባ የለበሱ አሻንጉሊቶች ናቸውና አይሰሟቸውም። ያም ሆኖ ግን የተከሰሱበትን መድረክ ለወያኔ ማጋለጫነት በመጠቀም ዳግም ጀግነነት ፈጽመዋል። አሁን በወያኔ እስር ቤቶች ሰቆቃ እንደሚፈፀም ምንም ምስጢርነት የሌለው አደባባይ የወጣ ሃቅ ሆኗል። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳም ለወራት ብቻዋን ጨለማ ቤት ውስጥ ታስራ ሴት መያዝ በማይገባት አሰቃቂ ሁኔታ እንድትቆይ በማድረግ የመንፈስ ጥንካሬዋን ለመስበር መሞከሩ ዓለም ያወቀው ሃቅ ነው። ዓለም ዓቀፍ ማኅበረሰብ ግን ሂትለራዊ ሰቆቃ ዛሬ በኢትዮጵያ እስር ቤቶች ውስጥ ተግባራዊ እየሆነ እንደሆነ እያወቀ ዝምታን መርጧል።

ወያኔ ያወጀብን አጠቃላይ ሽብር ሁሉንም ዜጋ የሰቆቃ ሰለባ እያደረገው ነው። ምርጫ ለኢትዮጵያዊያን የሰቆቃ ዑደት መገለጫ ሆኗል። "ወያኔ ለሚቀጥለው ምርጫ እየተዘጋጀ ነው" ማለት ገራፊዎቹን በየቦታውም እያሰማራ ነው ማለት ነው። "ምርጫው ተቃረበ" ማለት ሰቆቃው ተፋፍሟል ማለት ነው። "ምርጫው ደረሰ" ማለት ደግሞ ሰቆቃው ወደ ግድያ ተሸጋግሯል ማለት ነው። አሁን ምርጫ ተቃርቧል እናም የዜጎቻችን እንግልት የሚበረታበት ወቅት ነው። በዚህ ወር ብቻ ወደ አምስት መቶ የሚጠጉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት ታስረዋል። በየመንደሩ ደግሞ የዚህን ብዙ ጊዜ እጥፍ ብዛት ያላቸው ደጋፊዎች ታጉረው ስቃይ እየደረሰባቸው እንደሆነ መገመት ይቻላል።

ወያኔ ለጆሮ የሚሰቀጥጡ ሰቆቃዎችን እያደረሰ በቁስላችን ላይ ጨው ለመነስነስ እሱ ራሱ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ኮሚሽነር በመሆን ስለ ሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ይደሰኩራል፤ የእንባ ጠባቂ ኮሚሽነርም ሆኖ በመቅረብ የፈሰሰ እንባ የሌለ መሆኑን ለባእዳን ይናገራል። የሰቆቃ ሪፖርቶችን የማዳመጥ ፍላጎት ያላሳዩ የአንዳንድ አገሮች ዲፕሎማቶች ይባስ ብለው የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ ኮሚሽን እና የኢትዮጵያ እንባ ጠባቂ ኮሚሽን የተሰኙትን የወያኔ ተቋማትን ሪፖርት እንደ ገለልተኛ ታዛቢ አስተያየት ጆሮዓቸውን ሰጥተው በጥሞና ሲያዳምጡ ታዝበናል። የወያኔን የማስመሰል ድራማን እያወቁትም ያስተናግዱታል። በእነሱ ይሁንታ የልብ ልብ የተሰማው ወያኔ ቀጥቃጭ፣ ከሳሽ እና ፈራጅ ከመሆንም አልፎ ሰብዓዊ መብቶችን አስከባሪና እንባ አባሽ ነኝ እያለ ይቀልድብናል።

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነተና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ደጋግሞ እንደገለፀው ይህንን እኩይ ሥርዓት የማስወገድ ኋላፊነት የወደቀው የበደሉ ገፈት ቀማሽ በሆነው በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ነው። ይህን ግፍና ውርደት ማስቆም የሚችለው የተደራጀ የህዝብ ትግል ነው። በታሳሪዎች እና በሌላውም ህዝባችን ላይ እየተፈፀመ ያለው ሰቆቃ እንዲያበቃ ወያኔን ከሥልጣን ማባረርና በምትኩ ለሰብዓዊ መብቶች ክብር ያለው ፍትሃዊ ሥርዓት መመሥረት ይኖርበታል። ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነተና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ቆርጦ ተነስቷል፤ ለዚህም መላው ህዝብ በጋራ እንዲነሳ ጥሪ ያደርጋል።

ሰቆቃ ማድረስ በሰብዓዊነት ላይ የሚፈፀም ዓለም ዓቀፍ ወንጀል በመሆኑ ይዋል ይደር እንጂ የማይቀር እና በይቅርታ የማይታለፍ ተጠያቂነትን በውስጡ ይዞዓል። በዚህ ወንጀል የተሳተፉት ሁሉ መጠየቃቸው በፍጹም አይቀርም። ይህ ቀን ደግሞ በቅርቡ ይመጣል። የወያኔ በሥልጣን ላይ መቆየት እንኳን ከተጠያቂነት አያድናቸውም። ያኔ "ታዝዤ ነው የፈፀምኩት" ማለት ተቀባይነት አይኖረውም። ህሊና ያላችሁ ሁሉ እጃችሁን ከሰቆቃ መፈጸም አውጡ፤ ሰቆቃን አጋልጡ፣ ታገሉ። አለበለዚያ ግን የህዝብ ቁጣ በእናንተ ላይ የሚወርድበት ቀን ሩቅ አይደለም።

**"አገሬን ከሚመጣው አደጋ ለማዳን ስል እርምጃ መውሰድ ነበረብኝ" ጄ/ል ተፈራ ማሞ**

## "አገሬን ከሚመጣው አደጋ ለማዳን ..." ከገጽ 1 የዞረ

ጄ/ል ተፈራ፣ በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት፣ ከወያኔ ጎን ተሰልፈው አገራቸውን እየበደሉ ለሚገኙ የመከላከያ ፣ የፖሊስና የደህንነት አባላት፣ እንዲሁም ለወጣቶች ትልቅ አርያ እንደሚሆኑ ያነጋገርናቸው ሰዎች ገልጸውልናል።

በተያያዘ ዜናም በመፈንቅለ መንግሰት ሙከራ ከተከሰሱት እስረኞች መካከል የተወሰኑት እስረኞች በኤሌክትሪክ ማሞቂያ ይጠበሱ እንደነበር ለማወቅ ተችሎአል። ።

በዚህ መሳሪያ የተጠበሱ እስረኞች ከፍተኛ የሆነ ውስጣዊ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን የተገኘው መረጃ አመልክቶ፣ ስለሂደቱም ሲዘረዝር እንዲህ ይላል፤ "በመጀመሪያ እስረኞች በአንድ ክፍል ውስጥ እንዲገቡ ይደረጉና እጅግ ሀይለኛ ጉልበት ያለው የኤሌክትሪክ ማሞቂያ ይከፈትባቸዋል። ማሞቂያው እየጋለ ሲሄድም እስረኞቹ ከማሞቂያው በታች ቁጭ እንዲሉ ይደረጋሉ። በዚህን ጊዜ ማሞቂያው የሚያገኘው መሀል አናታቸውን ይሆናል ማለት ነው። እስረኞቹ ሙቀቱን ለተወሰኑ ደቂቃዎች እንደ ምንም ለመቋቋም ይሞክራሉ ፣ ብዙም ሳይቆዩ ግን ሀይላቸው እየተዳከመ ይመጣል፣ በመጨረሻም ራሳቸውን ስተው ይወድቃሉ። በዚህ መሳሪያ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ለመንቃት ብዙ ጊዜ ይወስድባቸዋል። መሳሪያው በውጭ አካላት ላይ ምንም አይነት ጠባሳ የማይተው ሲሆን፣ በውስጥ አካላት ላይ በተለይም በአንጎል ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያመጣል።"

## የኦርቶዶክስ አማኞች ቤ/ክርስቲያናቸውን ... ከገጽ 1 የዞረ

አምጥተው ለማሾም ይሰራሉ፣ በአገር ቤትና በውጭው አለም በአባ ጳውሎስ ላይ የሚቀጣጠለውን ተቃውሞ የሚመራውና የሚያስተባብረው ማህበረ ቅዱሳን ነው፣ በፓትሪያርኩ ላይ የሚቀርቡ ክሶችን እና ተቃውሞዎችን ማህበሩ አያወግዝም፣ ለማደራጀ መምሪያው አይታዘዝም፣ ባለፈው ግንቦት ሲኖዶሱ በአባ ጳውሎስ ዝርክርክ አሰራርና ሙስና ካሰማው ተቃውሞ ጀርባ የማህበረ ቅዱሳን እጅ አለበት" የሚሉት በዋናነት የሚጠቀሱ መሆናቸውን መረጃው አመልክቷል።

መረጃው በመስከረም 12/ 2002 አም በቤተክህነት ስለተደረገው ስብሰባ ላይ የነበረውን ሁኔታ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል " መስከረም 11፣ 2002 አም ከቤተክህነት ስልክ ተደውሎ ነገ ጧት በ2፡30 ላይ ቤተክህነት ግቢ ውስጥ ስብሰባ ስላለ እንደትመጡ የሚል ትእዛዝ ተላለፈ። በዚሁ እለት 11 ሰአት ተኩል ገደማ አባይ ጸሀየ፣ የደህንነት ሃለፊው፣ አባ ጳውሎስና አባ ሰረቀ ብርሀን ተገናኝተው ለብቻቸው አቋም መያዛቸውን መረጃዎች አፈትልከው ወጥተው ነበር። እነዚህ ሰዎች በማግስቱ ድራማውን ለመተወን እንደገና ተመካክረው ከአንድ ክፍል ውስጥ በጋራ ወጡ። በሁዋላ አባ ጳውሎስና አባ ሰረቀብርሀን ለማህበሩ ያላቸውን ጥላቻ ሲገልጹ፣ አባይ ጸሀየ ደግሞ የወያኔን ፍርሀት ገለጸ። የማህበሩ አባላት ግን በባለስልጣኑ የቀረቡትን ማስፈራሪያዎችና ክሶች ውድቅ አደረጉ። በመጨረሻም አባ ጳውሎስ የማነባት መግለጫ አለችኝ አሉና አንዲት ወረቀት አውጥተው አነበቡ። ይህ መግለጫም በቴሌቪዥን ተላለፈ። የማህበሩ ሰብሳቢ ቀሲስ ዶ/ር ሙሉጌታ ወዲያው ተነስቶ 'አሁን የተነበበው መግለጫ ማህበሩን የማይገልጽና የማንቀበለው ነው" ሲሉ በድፍረት ተናገሩ። የእርሳቸው መግለጫ ግን በቴሌቪዥን ሳይቀርብ ቀረ።" ብሏል።

ግንቦት 7 በሀይማኖቶች መካከል ግጭቶች እንዲነሱ እያደረገ ያለውን የወያኔን እኩይ ሴራ በተደጋጋሚ ሲያወግዝ መቆየቱ የሚታወስ ሲሆን፣ ኢትዮጵያን የሀይማኖት እኩልነት የተረጋገጠባትና ዜጎች በነጻነት የአምልኮ ስርአታቸውን የሚፈጽሙባት አገር ለማድረግ ብቸኛው መፍትሄ ወያኔን ማስወገድ መሆኑን ግንቦት7 በጽኑ ያምናል።

**በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን**

**የፖስታሳጥን ቁጥር ፡** POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 72 መስከረም 21 2002 ዓ.ም፤

# ምርጫ 2002 በተመለከተ የግንቦት 7 አቋም ማብራሪያ

ክፍል 2 ካለፈው የቀጠለ

## 2.2. ለመሆኑ ዓለም የሚያውቃቸው የእውነተኛ ውድድር ምርጫ መለያዎች ምንድር ናቸው?

ዲሞክራሲያዊ የምርጫ ሥርዓት የግድ ነፃ (free) ፍትሃዊና (fair) ተአማኒነት ያለው (credible) የፖለቲካ ሜዳ ተፈጥሮ፣ የፖለቲካ ቡድኖች የሚወዳደሩበት መድረክ ነው። ለዚህም፡-

- አስመራጩ (የምርጫ አስፈፃሚው) አካል ከአንድ ፓርቲ ቁጥጥርና ተጽእኖ ነጻ ሆኖ የተደራጀ፣ በነፃ አሠራርና በገለልተኛነት ሥነ ምግባር የዳበረ ቡድን መሆን አለበት፡፡
- የመንግሥት ሥልጣን በግልጽ በተደነገጉ በሥልጣን መባለግ እንዳይኖር በሚያደርጉ ሕጎች የተከፋፈለና ተጠያቂነት ያለበት፤ ይህም በተግባር የተመሠከረለት መሆን አለበት፡፡
- የአገሪቱ የፍትህ ሥርዓት በቅልጥፍና፤ በእኩልነትና ከሕግ አስፈጻሚው ነፃ በሆነ መልኩ ሲሠራ የታዬ መሆን አለበት፡፡
- የመንግሥት ወታደር፤ ፖሊስ፤ የፀጥታና እንዲሁም ሲቪል አስተዳደሩ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥጥር ውጭ መሆን አለበት፡፡
- የመንግሥት ሀብት ተቀናቃኝ ፓርቲዎችን ማዳከሚያ፣ በምርጫ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት መጠቀሚያ፣ ዜጎች የገዥው ፓርቲ አባላት እንዲሆኑ የመግዣና የማስገደጃ መሣሪያ መሆን የለበትም፡፡
- የመንግሥት ሚዲያም ለሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችና ለሁሉም ዜጎች መገልገያ በሚሆንበት መልኩ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ነጻና ገለልተኛ በሆነ መንገድ መደራጀት ይኖርበታል፡፡

እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት አገር እንኳን እንደ ወያኔ ባለ ለአስራ ስምንት ዓመታት በማጭበርበር የታወቀ ገዥ ቡድን ቀርቶ በሌሎችም ለዘብተኛ አገዛዞች በሚገኙባቸው አገሮች እንኳን ሃቀኛ ውድድር ያለበት ምርጫ ማድርግ እንደማይቻል ተደጋግሞ ታይቷል። ከእዚህ ተነስተን እስኪ ወያኔ በምርጫ ግጠሙኝ እያለ በተቃዋሚዎች ላይ የሚፏልልበት የአገራችንን ወቅታዊ የምርጫ ሁኔታ ምን እንደሚመስል እንመልከት፤

- አገራችን በመለስ ፈቃድ ብቻ የሚንቀሳቀስ የምርጫ ቦርድና መለስ እንዳሻው የሚሾማቸውና የሚሽራቸው የምርጫ ቦርድ አባላት አሏት፡፡ ከእነዚህም መሃል አብዛኛዎቹ የወያኔ ካድሬዎች ናቸው፡፡
- አገራችን በወያኔ በጎ ፈቃድ ብቻ የሚዘወር የወያኔ የፕሮፓጋንዳ መሣሪ የሆነ የፌደራልና የክልል መንግስታት መገናኛ ብዙሃን ያለባት አገር ናት፡፡ የግል የተባሉ ጥቂት ራድዮ ጣቢያዎች በሙሉ በወያኔ ካድሬዎችና በወያኔ ካፒታልና ፈቃድ የተቋቋሙ ናቸው፡፡ የግል ጋዜጦችም በወያኔ አፋኝ የፕሬስ ህግና የአፈና ተቋማት በነጻነት እንዳይዘግቡ የቀፈደዱ ናቸው፡፡
- አገራችን መለስ ዜናዊ በአንድ ቀን ውስጥ የፈለገውን (የገዛ ህገ-መንግሥቱን ጭምር የሚጥስ) ህግ ለማውጣት የሚያስችለው በመለስ የሚታዘዝ ፓርላማ ያለባት አገር ናት፡፡ መለስ ዜናዊ ለዳኞች ስልክ ደውሎ፣ የብይን ውሳኔያቸው ምን መሆን እንደሚገባው ትእዛዝ የሚሰጥባት ሃገር ናት፡፡ ዳኞች፣ አቃቤ ህጎችና መረጃ አቅራቢ ፖሊሶች በሙሉ የወያኔ ካድሬዎች ናቸው፡፡
- አገራችን፣ መለስ የምርጫ ውጤት ካልተስማማው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚያውጅባት፣ በመለስ ትእዛዝ ሰላማዊ ስልፈኞችን እያነጣጠረ ግንባርና ልብ ላይ የሚተኩስ ነብሰ ገዳይ፣ ልዩ ጦር መኖሩ በግልጽ የታየባት አገር ናት፡፡
- ከሁሉም በላይ ሃገራችን በግምት ሳይሆን በተግባር በምርጫ 97 እንደታየው፤ ነፃ ምርጫ ከተደረገ የወያኔ መንግሥት ከስልጣን ሊወገድ የሚችልባት አገር ናት።

ከላይ የጠቀስናቸው ነጥቦች በአገራችን ነጻና ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ፣ ፕሬስ፣ የፍትህ ሥርዓት፣ የፖሊስ፣ የደህንነትና የመከላከያ ኃይል አለመኖራቸውን የሚረጋግጥ ነው፡፡ እነዚህ ተቋማት የሉም ማለት ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ሊኖር አይችልም ማለት ነው፡፡ ይህ ድምዳሜ በሂሳብ 1 ሲደምር 1 ሁለት ይሆናል ከሚለው ሎጂክ ምንም ልዩነት የሌለው ነው፡፡ በምንም ምክንያት የሚለወጥና የሚቀየር አይደለም፡፡ የመጨረሻው ነጥብ ደግሞ የሚያሳየን፤ እውነተኛ የሕዝብ ወገን የሆኑ ሁሉ በኢትዮጵያ ስለምርጫ ሲያስቡ የማሸነፍ እድላቸው በተግባር የታየና የሚቻል መሆኑን እራሳቸውም አምነው ለሕዝቡም ይህንን ሁኔታ በመግለጽ መሳተፍ የሚገባቸው መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ የማሸነፍ እድላቸው ዛሬ ጠቦ የሚታየው ወያኔ ከግንቦቱ 1997 ምርጫ በኋላ የወሰዳቸው የእመቃ እርምጃዎች ውጤት እንጂ ድርጅቶቹ ከወያኔ በማነሳቸው ህዝቡም ወያኔ ላይ የነበረው ምሬት በድንገት ወደ ፍቅር በመቀየሩ እንዳልሆነ ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ከእዚህ ተነስተው ለማናሸንፍበት ምርጫ ለምን እንገባለን የሚል የተስፋ መቁረጥ አቋም ከመውሰዳቸው ወይም ለማናሸንፍበት ምርጫ ወያኔን የወሰነልን ወንበር ተቀብልን መሰንበት የሚል አደገኛ ውሳኔ ላይ ከመድረሳቸው በፊት በነጻና በፍትሃዊ ምርጫ ወያኔን ከሥልጣን ማባረር እንደሚችሉ በራሳቸው መተማመን ይኖርባቸዋል፡፡ ምርጫ 97 ያስተማረን ቁም ነገር ቢኖር በተቃዋሚዎች ላይ ትልቅ ንቀት የነበረው ወያኔ በራሱ ተማምኖ በከፈታት የዴሞክራሲ ቀዳዳ ተቃዋሚዎች ወያኔን በቀላሉ ከሥልጣን ሊያባርሩት እንደሚችሉ ነው፡፡ ችግሩ ያለው የዴሞክራሲ ምህዳሩ መጥበብ ላይ እንጂ ህዝብ በወያኔ ላይ መማረሩን ስላቆመ እንዳልሆነ መተማመን ያስፈልጋል፡፡ ሕዝብ የነጻ ምርጫ እድል ቢሰጠው አሁንም ከ1997ቱ በከፋ መልኩ ወያኔን የሚተፋወ መሆኑን መገንዝብ ተገቢ ነው፡፡ የዴሞክራሲ ምህዳሩ ቢሰፋ የነጻና የፍትሃዊ ምርጫ ሂደት ቢጀመር ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአጭር ግዜ ውስጥ ተሰባሰበው በጋራ ወያኔን ገጥመው ሊያሸንፉት የሚችሉበትን መርሃ ግብር መዘርጋት፣ የሕዝብንም ድጋፍ ማግኘት እንደሚችሉ በራሳቸው ላይ መተማመን ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህ በተግባር በ1997ቱ ምርጫ የታየ ሰለሆነ ተቃዋሚዎች ወያኔ የሚነዛውን የቅስም ሰበራ ፕሮፖጋንዳና ጭቆና ራሳቸውም ሆኑ ሕዝብ መቋቋም እንዲችል በጋራ መታገል ይኖርባቸዋል። በተጻራሪው መንግሥት አሁን ካለው የመጨቆን አቅም ተነስተው ግን ማሸነፍ እንደማይቻል ማሰብ ትልቅ ስህተት ነው። ከዚህ የተሸናፊነት መንፈስም በመነሳት የመለስ-በረከት ቡድን አስልቶ የፈቀደልንን ወንበር መያዝ መሻሻል ነው ብለው ካሰቡ ደግሞ የከፋ ስህተት ይፈጽማሉ፡፡ እንዲህ አይነቱ ውሳኔ የሀገሪቱን ሁኔታና የሕዝብን ፍላጎትና ችሎታ አለመረዳት ይሆናል። ሰመ-ጥሩ የተቃዋሚ ሰዎች ወያኔን አጅበው ለወያኔ አሸናፊነት በተመቻቸ ምርጫ ከገቡ የዚህ ተግባር ዋና ውጤቱ በሀገራችን ውስጥ በዘር መድሎና በአምባገነንነት ላይ የተዘረጋውን ሥርዓት እድሜ ማራዘም ይሆናል።

## 3. ወያኔና የ2002 ምርጫ

የ2002ቱ ምርጫ ገና አንድ ድምፅ ከመሰጠቱ በፊት ወያኔ አሸናፊነቱን የተረጋገጠ ለማድረግ በሁለት ምዕራፎች የተከፋፈለ መርሃ ግብር ነድፎ መነቃነቅ ከጀመረ ሰንብቷል። የመጀመሪያው ምዕራፍ የተቃዋሚ ኃይሎችንና የሲቪል ማኅበራትን ማዳከም እና የሕዝብን ቅስም መስበር ሲሆን፤ ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ እራሱ መጥኖ በሚከፍታት ጊዜና ሁኔታ የአስመሳይ ምርጫ "ውድድርን" ማኪያሄድ ነው።

ተቃዋሚዎችን በማዳከም ዙሪያ ወያኔ እስካሁን ያደረጋቸው ዋና ዋና እርምጃዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ፤

- ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ደግፈዋል፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በአመራርነትና በአባልነት አገልግለዋል ባላቸው ላይ የግድያ፣ የእሥራትና የማሳደድ ውርጅብኝ አውርዷል፡፡ ወያኔን ክፍኛ ያስደነገጠውን ትልቁን የፖለቲካ ድርጅት ቅንጅትን አፍርሶ, የመሪዎችን የፖለቲካ ነጻነት ሸምግልና በሚል ሽፍጥ ገድቦ፤ እንኳን ለነጻና ፍትሃዊ ምርጫ መካሄድ አስፈላጊ የሆኑትን የተቋማት ጥያቄዎች ማነሳት ቀርቶ እነሆ ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳን ውሸትን እውነት ካላልሽ ብሎ ወህኒ ወርውሯት እያየን ነው፡፡
- የአገዛዙ የፀጥታ ኃይል የተቃዋሚ ድርጅቶች በየጽሕፈት ቤታቸውና በየክልሉ ያሰማሯቸውን ሠራተኞችና አስተባባሪዎች በገንዘብ በመደለል፤ በማስፈራራትና ከዚያም አልፎ በማሠር ድርጅቶችን ያለ አደራጆች ለማስቀረት በየቀኑ ወንጀል እየፈጸመ ነው።
- ለተቃዋሚዎች ቤትን የሚያከራይ ማስጠንቀቂያና እንግልት ሲደርስብት፤ ይህንንም እየፈራ ቤቱንና የመስብሰቢያ ቦታዎችን ለተቃዋሚዎች አናከራይም የሚለው ባለ ሀብት ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ ነው።
- ተቃዋሚዎች በየጊዜው ለሚጠይቁት ሕዝብን በአደባባይ የመሰብሰብ ጥያቄ በየምክንያቱ «አይቻልም» የሚል ምላሽ መስጠት የተለመደ ነው። በዚህ ተደጋጋሚ ክልከላ ሳይሰላቹ በጥያቄ ብዛት ስብሰባ በተወሰነ ቦታ የሚፈቀድላቸው ተቃዋሚዎች ደግሞ የተስበሰበውን ሕዝብ ለማሸማቀቅና ከዚህ በፊት እንደታየውም ለስለላ ሥራ ለማዋል የመንግሥት "ጋዜጠኞች" ስብሰባውን ከመጀመሪውያ እስከመጨረሻው፣ በእንያዳንዱ ተሰብሳቢ ፊት ላይ እያነጣጠሩ በቪዲዮ ይቀርጻሉ። *(እነዚህ "ጋዜጠኛ" ተብየዎች የቀዱትን ስብስባ ለአንዲት ሰከንድ እንኳ በመገናኛ ብዙሃን ሲያሰሙት አይታይም።*
- የታወቁ የተቃዋሚ ድርጅቶችን የከፍተኛ አመራር ስብስባ ሂደቶችን የመንግሥት የስለላ ቡድኖች በተደበቁ ኤሌክትሮኒክስ መቅጃዎች በመቅረፅ፣ በስለላ ክፍሉ በነፃ ጋዜጣ ስም በተቋቋሙ ጋዜጦች ለሕዝብ በማቅረብ በተቃዋሚ መሪዎች መካከል አለመተማመንን ለመፍጠርና ከዛም አልፎ የተቃዋሚ መሪዎችን በሕዝብ ፊት ደካማ አድርጎ ለማሳየት አገዛዙ ሥራዬ ብሎ ተያይዞቷል።

በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ባላነሰ ሁኔታ ለዲሞክራቲክ የፖለቲካ ሕይወት እስትንፋስ የሆኑትን የሲቪኽ ማህበራትንና የነፃ ፕሬስን ለማዳካም ከወሰዳቸው እርምጃዎች በትንሹ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፤

- የስቪክ ማኅበራትን ነፃና ገለለተኛ አሠራር ጨርሶ የሚያጠፉ ሕግ እንደ ሎሌው በሚያዘው ፓርላማ አማካኝነት ደንግጓል። በተመሳስይ ሁኔታም ወያኔ የነፃ ፕሬሱ ሕዝቡን የሚያገለግልበትን መንገድ በሕግ አጥሯል፡፡
- በቅርቡ ደግሞ ይባስ ብሎ ሕዝቡን የማሰብ ነፃቱን እንኳን የሚጻረር "ጸረ-ሽብርተኛ" የተሰኘ ሕግ በእዛው የመለስ መሃተም ሆኖ በሚገለግለው ፓርላማ አጸድቋል።
- ይህም ሳይበቃው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይነተኛ ወያኔን መቃወሚያ የሆነውን ሰንደቃላማውን ማውለብለብ እንኳን ሕገ-ወጥ የሚያደርግ ሕግ በአሁኑ ሰዓት እያረቀቀ ነው።

በመጨረሻም ሕዝብ በምርጫ ለውጥ ይቻላል የሚለውን እምነት ጨርሶ ከአዕምሮው አውጥቶ በምትኩ የሕዝቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ ከወያኔ በጎ ፈቃድ ጋር እንደተያያዘ ቆጥሮ በፍርሃት እንዲወጥ የኢኮኖሚ፤ የፖለቲካና የስነልቦና ጦርነት ያለማቋረጥ ተደርጎበታል፡፡ **ክፍል 3 በሚቀጥለው ሳምንት ይቀርባል**

## የድንበር ጉዳይ ኮሚቴው የወያኔን . . . ከገጽ 1 የዞረ

ለተያዘው በየትኛውም ቦታ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በስልክ፣ በደብዳቤ፣ በኢሜል፣ እና በሌላም በሚቻለው መንገድ ሁሉ በስተጀርባቸው የሚሰራባቸውን ክህደትና ሴራ እንዲገነዘቡና ያንን ለመቋቋም እርምጃ እንዲወስዱ" ሲል ጠይቋል።

በመጨረሻም ኮሚቴው በአካባቢው ስለሚገኙ ነዋሪዎች የሚከተለውን መልእክት አስተላልፏል " በድንበሩ አካባቢ ያሉ ወገኖቻችን ከቤታቸው፣ ከከብት ግጦሽ ማሰማሪያቸውና ከእርሻ ቦታቸው ተፈናቅለው በከፍተኛ እንግልት ላይ ይገኛሉ።ከእነርሱ ውጭ ጥቂቶቹ የመሬታቸውንና የአገራቸውን ድንበር ለማስከበር ሲሉ እስከ አፍንጫቸው ከታጠቁ ሁለት ጨካኝ መንግስታት ጋር በመተናነቅ ከፍተኛ መስዋትነት በመክፈል ላይ ናቸው። ሁላችንም የነዚህ ወገኖቻችንን እሮሮ ላልሰሙት ወገኖቻችንና ለአለም ህብረተሰብ ማሰማት ኢትዮጵያዊ ግዴታ አለብን።"

ለሱዳን የሚሰጠው መሬት በትልቅነቱ የጅቡቲን ወይም የሩዋንዳን ወይም የቡሩንዲን የቆዳ ስፋት በሶስት እጥፍ የሚበልጥ ሲሆን፣ ከሆላንድ ወይም ከቤልጂየም የቆዳ ስፋት ጋር ሲነጻጸር ደግሞ በሁለት እጥፍ ይበልጣል። የወያኔ አምባገነኖች የስልጣን እድሜያቸውን ለማራዘም በማሰብ ይህን የሚያክል ሰፊ መሬት ለሱዳን መስጠታቸው፣ ገገሮቹ ለኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ሉአላዊነት ደንታ እንደሌላቸው ያሳያል የሚሉ አስተያየቶችም በመደመጥ ላይ ሲሆኑ፣ የወያኔ አምባገነኖች በሀይል ከስልጣናቸው ሲሽቀነጠሩ በሁለቱ አገሮች መካከል ጦርነት ሊቀሰቅስ የሚችል ነገር መሆኑንም ባለሙያዎች በመናገር ላይ ናቸው። አሁን ያለው ትውልድ የአባቶቹንና የእናቶቹን የአደራ ቃል በመረከብ አገሩን ከገባችበት ውርደት መታደግ እንዳለበት የገለጹት ደግሞ አባት አርበኛ ሽበሺ ለማ ናቸው። አባት አርበኛ ሺበሺ የወያኔ አምባገነኖች የሚሰሩት እኩይ ስራ ምንጊዜም እንደሚያሳዝናቸውና እንደሚያበሳጫቸው ገልጸው፣ ወጣቱ ትውልድ የአገሩን ዳር ድንበር ለማስከበር አለመቻሉ እንዳሳዘናቸውም ሳይሸሽጉ ተናግረዋል። "ኢትዮጵያ የማንንም መሬት አትመኝም የራሱዋንም አትሰጥም" የሚሉት አርበኛ ሺበሺ፣ በወያኔ የጉድ ዘመን እያየነው ያለነው ነገር ሁሉ ለማመንም የሚያስቸግር ነው ብለዋል።

## መለስ ዜናዊ ለዓለም አቀፍ ወንጀለኞች ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ተጠየቀ

በአሜሪካዋ የፒተርስበርግ ከተማ በተደረገው የተቃውሞ ሰልፍ ላይ ኢትዮጵያውያኑ የምእራብ አገሮች መንግስታት በነፍሰገዳይነቱና በዘረኛነቱ የሚታወቀውን የመለስ ዜናዊን አገዛዝ እንዲያወግዙ ጠይቀዋል። "የታሰሩት ፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ! ብርቱካን ሚደቅሳ ትፈታ !የመለስ ዜናዊ በዚህ አለም አቀፍ ስብሰባ መገኘትን አንቃወማለን! መለስ ዜናዊ አሳፈሪ መሪ ነው! መለስ ዜናዊ ገዳይ ነው፣ መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው፣ መለስ ዜናዊ ዘረኛ ነው" የሚሉትን መፈክሮች ሲያሰሙ የነበሩት ኢትዮጵያውያኑ፣ ምእራባዊያን መንግስታት ድጋፋቸውን እንዲያቋርጡ ጠይቀዋል።

የቡድን 20 አገሮች ባደረጉት ስብሰባ ላይ በተመልካችነት የተጋበዘው አምባገነኑና ዘረኛው መለስ ዜናዊ፣ ኢትዮጵያን በድህነት አረንቋ ውስጥ በመክተቱ፣ ዲሞክራሲን በማፈኑና ዘረኝነትን በማስፋፋቱ የሚታወቅ ሲሆን፣ የትናንት በስቲያው የኢትዮጵያውያን ተቃውሞም ይህን እውነታ አጉልቶ የሚያሳይ ነበር።

በተያያዘ ዜና መለስ ዜናዊና ባለቤቱ አዜብ መስፍን አሜሪካዊው ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ባዘጋጁት የራት ግብዣ ላይ ሲገኙ፣ አንድ እንግዳ ነገር ተፈጥሮ እንደነበር የኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጠኛ ሄለን ኩፐር ዘግባለች። "ፕሬዚዳንት ኦባማ የሁሉንም አገሮች መሪዎች እንኳን ደህና መጣችሁ እያሉ ሲቀበሉ፣ የኢትዮጵያው ገገር መለስ ዜናዊ ተራ ደረሰ" ትላለች ጋዜጠኛዋ "መለስ ዜናዊ መኪናው ወስጥ ሚስቱን በሆነ ነገር ሳያበሳጫት አልቀረም። ልክ ፕሬዚዳንቱን ሊጨብጡ ሲሄዱ አዜብ በባሏ ላይ አይኗን አፈጠጠችበት፤ ሚ/ር ኦባማና ባለቤታቸው ምን እንደተፈጠረ ለማወቅ አልቻሉም። በነገሩ ግራ ተጋብተው ተፋጠጡ፤ እንደማይገፈግም አሉ። ደግነቱ ቶሎ የኦባማን እጅ ጨብጠው ወደ ውስጥ ገቡ። መለስ ሚስቱን መኪና ወስጥ በሆነ ነገር አበሳጭቷታል።" ብላለች ጋዜጠኛ ሄለን።

ባራክ ኦባማ መስከረም 13 2002 ዓ.ም በተባበሩት መንግስት ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር ህዝባቸውን በጉልበት የሚገዙ፡ የሚያሰቃዩና በሙስና የተጨማለቁ የታዳጊ አገር መሪዎች ድህነትንና አድልዎን ከምድራችን ለማስወገድ ለሚደረገው አለም አቀፍ ጥረት እንቅፋቶች ብቻ ሳይሆኑ ከዘመኑ ስልጣኔ የራቁ እጅግ ኋላ ቀሮች በመሆናቸው በተሳሳተ የታሪክ ጎዳና ላይ ናቸው በማለት እንደመለስ ዜናዊ ዓይነቱን ኋላ ቀር ዘረኛ እንዳሸማቀቁ ይታወሳል። ለመብታቸውና ለነጻነታቸው መከበር ከአምባገነን ሥርዓቶች ጋር የሚፋለሙትን ህዝቦች ትግልም አገራቸው አሜሪካ እንደምትደግፍ ሳይደብቁ ተናግረዋል።

## በተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና . . . ከገጽ 1 የዞረ

ብለህ ተናገር ተብለው በወያኔ ካድሬዎች ሲጠየቁ፣ አዛውንቱም "እንገቴን ቆርጣችሁ ትጥላላችሁ እንጅ ለሰላምና ለፍትህ መስፈን ትግል የሚያደርገውን ፓርቲየን በዚህ አየነት አጉል ውንጀላ አላወግዝም" ማለታቸውን የአንድነት ፓርቲ ምንጮች ለዘጋቢያችን አስታውቀዋል።

የወያኔ መሪዎች፣ በእነ ጀነራል ተፈራ ማሞ ተባባሪነት፣ ግንቦት7 የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ለማድረግ ሰዎችን በህቡዕ አደራጅቶአል የሚል ክስ ካቀረቡበት ያለፈው ሚያዚያ ወር ጀምሮ፣ በአዲስ አበባና በሌሎችም ትላልቅ ከተሞች ህብረተሰቡን በፍርሃት ለማሸማቀቅ ብዙ ያላቸውን ሰላዮችና ፖሊሶች ያሰማሩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። የወያኔ ባለስልጣኖች አሁን አሁን የቅርብ የሚሏቸውን ሰዎች ሳይቀር እየተጠራጠሩ በመምጣት ላይ መሆናቸው የታወቀ ሲሆን፣ ምናልባትም ከመጪው የይስሙላ ምርጫ በሁዋላ በርካታ የአማራና የኦሮሚያ ተወላጅ የወያኔ ባለስልጣናት በአዲሶቹ የሁለቱ ብሄር ታማኝ አገልጋዮች ሊተኩ እንደሚችሉ ፍንጮች በመታየት ላይ ናቸው።

የግንቦት 7 ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ምንም አማራጭ አጥተው ወያኔን በተለያየ መስክ የሚያገለግሉ ሁሉ ለነጻነት የሚደረገውን ትግል በማገዝ ከታሪክ ተጠያቂነት እራሳቸውን እንዲያነጹ በዘንድሮው የአዲስ አመት ንግግራቸው ጥሪ ማስተላለፋቸው ይታወቃል።

## ግንቦት ነዉ ጠላትህ

አታመጣዉ የለህ አትቀላምደዉ
መፍትሄ አይሆንህም ጠላትህ ግንቦት ነዉ

እሱዉ ነዉ ያመጣህ እየገፈተረ
የንፁሃንን ደም ምስ እየገበረ

አዉሎ አከራርሞ ብቅ አለብህ ድንገት
የዛሬ አምስት ዓመት ልክ በግንቦት ሰባት

ህዝቡን አስጨንቀህ ጎትጉተህ ጎትጉተህ
ዉጣ ድምፅህን ስጥ ነፃ ነፃ ብለህ
ምንም ሳያቅማማ ስሜቱን ነገረህ
ግራ ብትጋባ ማሰሩ ቀለለህ፣

መግደል ማሳደዱ ማቆም ከቸሎት
አልሆንም መፍትሄ ያንተ መድሃኒት

አመቀዉ ብሶቱን ዉስጥ ዉስጡን ተብላላ
እንዲህ ሲከራርም ገንፍሎ ሊፈላ

ያባንንህ ገባ አልቀረም ቀዝቅዞ
የያዘህ አባዜ ናላህን አናዉዞ

ግንባር ፈጠሩብህ አልሰራም ተነኮሉ
ለዚህ ያበቃንን ጦሰኛ እየጠሉ

እናም ተጠራሩ አያድራትም ብለዉ
አንድነት ከሚለዉ ከምንሊክ ግቢዉ

ይወጣል ተገፍቶ ከዚያስ አይከረማትም
በአቋምህ ፅና ወገን አትዳከም

ጠላትህ አንድ ነዉ ኃይል አይበታተን
ይልቅ ተቀናጅተህ አሳየዉ ክንድህን

ዓመት ዞሮ ገጥሞ ቢያልፍም በልማዱ
የልቤ አልደረሰም አልፀዳም መንገዱ

ቆሻሻዉ ተንፍጎ አገር እያገማ
ማነዉ ጀርባ የሚያይ ማነዉ የሚያቅማማ

**ግንቦት!**

እሱዉ ነዉ ጠላትህ እኛ ምን እናርግህ
ብታስር ብትገርፈንም የለን የምንሰጥህ

ፀብህ ከእኛ አይደለም ከዘመን ከወር ነዉ
አማራጭ የለህም እሱኑ ለምነዉ

አትጋፋ ከሰዉ ቀን ጨልሞብሃል
ብርሃኑ ሳለ መጓዙን ጠልተሃል
ቃሉም እንዲህ ይላል

ብርሃን ከጨለማ ምኑን ህብረት አለዉ
ቦግ ባለ ጨረር መሰወር ከንቱ ነዉ
ይልቅ ልብ ገዝተህ እሱን ተማፀነዉ፣

ጠላትህ ግንቦት ነዉ እንዲሁ አይለቅህም
ይጠራርግሃል ወደድከም ጠላህም
ግንቦት እንዳስገባህ እሱዉ ያስወጣሃል
እንጃ መከረምህን ከደጃፍህ ቆሟል።


## የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ

### የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ፃይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org